

4. **ቱሪዝም ብዝሃነትን ያከብራል››**

(Tourism Celebrating Diversity)

ይህ መሪ መፈክር ለዘንድሮው ዓመት (እ.አ.አ. ለ2009) የተመረጠ መሪ ቃል ሲሆን በዓሉ በዓለም አቀፍ ደረጃ በአፍሪካ ጋና ለ30ኛ ጊዜ ይከበራል፡፡ የዘንድሮው በዓል ሁለቱን ዋነኛ የቱሪዝም ገጽታዎች ልማትና አንድነትን/ Development & unity/ ለማስተዋወቅ ጥሩ እድል እንደሆነ ይታሰባል፡፡ የዘንድሮው የዓለም ቱሪዝም ቀን በሃገራችን ኢትዮጵያ ለ22ኛ ጊዜ የሚከበር ነው፡፡ ይኸው 22ኛው ሀገር ዓቀፍ የዓለም ቱሪዝም ቀን በዓል ለዓመቱ መሪ መፈክር በአንጻሩ ትክክለኛ ትርጉም ምሳሽ ሰጪ በሆነው የደቡብ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ውስጥ ይከበራል፡፡

የዓመቱ መሪ መፈክር የሚያተኩረው በዓለም ብዝሀ-ባህላዊ ሀብቶች/እሴቶች እና ዘላቂ የቱሪዝም እንቅስቃሴ አካባቢያዊ ወግና ልማዶችን በማነቃቃትና እንዲያድጉ በማድረግ በኩል በሚጫወተው ሚና ላይ ነው፡፡

በዓለም ውስጥ ብዙ የተለያዩ ዓይነት አካባቢያዊ ስልጣኔዎች፣ ልምዶች፣ ወጎች፣ ባህሎች በአንድነት በሰላማዊ ሁኔታ ይኖራሉ፡፡

እነዚህም ብዙ አይነት ቋንቋዎች፣ ሀይማኖቶች፣ ስነጥበቦች፣ ምግብ፣ ፖለቲካ፣ ተፈጥሮአዊ፣ ታሪካዊና ባህላዊ አካባቢዎች ወዘተ ያጠቃልላሉ፡፡ ይህም ሰፊ የዓለም ሀብት/ብዝሀነት/ የቱሪዝም እንቅስቃሴውን ወይም ኢንደስትሪው እንዲያድግና የዓለም ትልቁ የኤክስፖርት ኢንደስትሪ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

እያንዳንዱ የዓለም ክልል በተለይም በማደግ ላይ የሚገኙ ሀገሮች የራሳቸው የሆነ ልዩ ገጽታና ይዘት አላቸው ይህም ለቱሪዝሙ ኢንደስትሪ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክት ነው፡፡

በዚህ መሠረት የዘንድሮውም የዓለም ቱሪዝም ቀን መሪ መፈክር ትርጓሜ ቱሪዝም ለብዝሀነት ብዝሀነት ለቱሪዝም ያላቸውን ተደጋጋፊነት የሚያሳይ ሲሆን ይኸው የዓለም ብዝሀነት ለዓመታት ለጉዞና ቱሪዝም ዕድገት እንደ መሠረት መሆኑን ያሳያል ፡፡ .
ስለዚህ ዘላቂ የቱሪዝም ኢንደስትሪ ልማትን ማረጋገጥና የዓለምን ልዩ ገጽታዎች /ብዝሀነትን/ መንከባከብና መጠበቅ የኛ ኃላፊነት ነው፡፡



ምስል 5. ጎብኚዎች በኦሞ ወንዝላ ይ (ደቡብ ኦሞ-ኦሞራቴ)

Southern Nations
Nationalities & People's
Regional State
Trade Industry Bureau
Culture and Tourism Development Process



ምስል 1. የ2009 የዓለም ቱሪዝም ቀን ሎጎ



ምስል.2. የሀመር ሴቶች በገበያ ቀን (ደቡብ ኦሞ)

e-mail south_tourism@yahoo.com
www.southtourism.gov.et
P.o.box 1078
Tell 251462210480/208490

## የዓለም ቱሪዝም ቀን

የዓለም የቱሪዝም ቀን በየዓመቱ መስከረም 17 (/ September 27 ) ቀን  የዓለም ቱሪዝም ድርጅት የሚየያወጣውን ዓመታዊ መሪ መፈክር መሠረት በማድረግ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ በአንድ በተመረጠ አህጉር ሀገርና በሁሉም አባል ሀገር ህዝቦች በተለያየ የጉዞ፤ የጉብኝት፣ የፓናል ውይይት፣ በባህላዊ ክንዋኔዎችንና ሌሎች ፕሮግራሞችን በማዘጋጀትና መስህቦችን በመጎብኘት የበዓሉ ሳምንት ይከበራል፡፡

የዓለም ቱሪዝም ቀን በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲከበር የተወሰነው በ1979 በስፔን አገር በተካሄደው የዓለም ቱሪዝም ድርጅት አባል ሀገሮች 3ኛ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ነበር፡፡ ይህ በዓል በየዓመቱ እንዲከበር ሀሳቡን የጠነሰሱት የዓለም አቀፍ አፌሴላዊ የጉዞ ድርጅት ህብረት (IVTO) አባላት ናቸው::

የዓለም ቱሪዝም  ቀን በዓል ዋነኛ ዓላማዎች፡-

1. ስለ ቱሪዝም አስፈላጊነትና መስኩ የሚሰጠውን ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካል ጠቀሜታዎችን በተመለከተ የዓለምአቀፉ ማህበረሰብ ያለውን ግንዛቤ ለማሳደግና፣

2. የዓለም ህዝቦችን በማቀራረብ በመካከላቸው መግባባትና መተዋወቅን በመፍጠር ለዓለም ሰላም፣ መተባበርና የጋራ ዕድገት  አስተዋጽኦ  ማበርከት የሚሉት ናቸው፡፡

የዓለም ቱሪዝም ድርጅት  ህብረተሰቡ ስለ ቱሪዝም የተሻለ ግንዛቤን ማግኘት እንዲችል እ.አ.አ ከ1980 ጀምሮ በየዓመቱ ትርጉም ያላቸው ዓመታዊ መሪ መፈክሮችን በማዘጋጀት በዓሉ በመሪ ቃሉ መሠረት እንዲከበር ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ በዓለም የቱሪዝም ድርጅት ዓማካይነት የወጡ ዓመታዊ የዓለም ቱሪዝም ቀን



ምስል.3. ጎብኚዎች በሀዋሳ ሀይቅ

መሪ መፈክሮችና መልዕክቶቻቸው ከዚህ በመቀጠል ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

### 1. ‹‹ቱሪዝም ያበለጽጋል›› (Tourism enriches)፡

ይህ መሪ መፈክር እ.አ.አ. 2006 26ኘውን የዓለም ቱሪዝም ቀን የተከበረበት ሲሆን መሪ መፈክሩ ቱሪዝም ለዓለም ህብረተሰብ የሚያበረክተውን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ትምህርታዊ፣ ባህላዊና ፖለቲካዊ ፋይዳዎች እንዲሁም የግለሰቦችንና የእያንዳንዱን ቤተሰብ ኑሮ ከማሻሻል አንጻር የሚጫወተውን ሚና መሠረት በማድረግ የተቀረፀ ነበር፡፡

### 2. ቱሪዝም ሴቶችን ተጠቃሚ ያደርጋል (Tourism Open Door For Women)

ይህ መሪ መፈክር እ.አ.አ በ2007 ለ27ኛ ጊዜ ለተከበረው  የዓለም ቱሪዝም ቀን የወጣ ሲሆን የመፈክሩ ዋና ዓላማ በቱሪዝም ሴክተር ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ በተመለከተ፣ የተገኙ ውጤቶችን፣ መልካም አጋጣሚዎችን፣ ፈታኝ ሁኔታዎችን፣ እንዲሁም የፆታ እኩልነትና ሴቶች የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው የሚወስኑበት መንገድ አጉልቶ ለማሣየትና ለተግባራዊነቱ ድጋፍ ለመስጠት  ታስቦ የወጣ ነበር፡፡



ምስል 4. የአንድራቻ መዳህ-ኒያለም

### 3. ቱሪዝም ለፈታኙ የዓለም አየር ንብረት ለውጥ መፍትሔ ያበረክታል (Tourism፡ Responds for the Challenge of climate change)

ይህ መሪ መፈክር እ.አ.አ በ2008  ለተከበረው የዓለም ቱሪዝም ቀን የተመረጠ መሪ መፈክር የነበረ ሲሆን የመፈክሩ ዋና ዓላማ ሀገራት የአየር ንብረት ለውጥንና ችግሮችን ለመከላከል እየደረጉ ያሉትን ጥረት ለመደገፍና ለችግሩ የመፍትሔ ሃሳብ በማመንጨት በኩል የቱሪዝሙ እንቅስቃሴ ጉልህ ሚና መጫወት እንደሚችል ለማሳየት ነው፡፡